# በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

# በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት




# የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት

**በኢንቨስትመንትና ምግብ ፓርኮች ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**

**የካቲት 2009 ዓ.ም**

**ቢሾፍቱ**

**ማውጫ** **ገፅ**

1. መግቢያ ........ 1
2. ዓላማ ........ 2
5. በንዑስ ዘርፉ የተሰማሩ መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ ኢንደስትሪዎች መረጃ ........ 3
5.1 በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ያልጀመሩ(ማልማት ያልቻሉ) ፕሮጀክቶች መረጃ ........ 3
5.2 ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ ........ 5
5.3 በትግራይ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ ........ 6
5.4. በአማራ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ ........ 7
5.5 በሀረሪ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ ........ 9
5.6 በደቡብ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ ........ 10
6. በ2009 ዓ.ም ሁለተኛ ግማሽ ዓመት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት እርምጃ ለመውሰድ የተለዩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ........ 12
7. የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ባልጀመሩ በፕሮጀክቶቹ ባለቤቶች የሚነሱ ዋና ዋና ምክንያቶች/ችግሮች ........ 13
8. በየክልሉ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ባልጀመሩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት በሚደረግ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የፍትሄ እርምጃዎች ........ 13
8.1. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ........ 13
8.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 14
8. ማጠቃለያና አስተያየት ........ 14

# 1. መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ልማቷንና ዕድገቷን ለማፋጠን ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች በሆኗ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ይህንኑ እንቅስቃሴ በማጠናከር በንዑስ ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶችን ለማበረታታት በሀገርም ሆነ በክልል ደረጃ የኢንቨስትመንት መሬት በቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጎ ለብዙ ባለበሀቶች አስፈላጊውን ድገፍ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገቡ በማስቻል ውጤታማ ማድረግ ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትም  በንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ ባለሀብቶችና ተዋንያኖች በአቅም ግንባታ፣በግብይትና ኢንቨስትመንት ሁለንተናዊ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል፡፡ በተለይም የንዑስ ዘርፉ ኤክስፖርት ምርቶችን ትኩረት በመስጠትና በጠንካራ መሰረት ላይ በመገንባት የውጭ ምንዛሪ በማምጣት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት መፋጠንና የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ከፍ ለማድረግ የቡድን ሥራን በጠናከር እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተገለጸው በንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ሁለንተናዊ ድጋፎችን በማድረግ ለውጤታማነታቸው ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ውጤታማ የሆኑ የንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎችም ለሀገራችን የማይናቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል እንደማንኛውም ባለሀብት አስፈላጊው ድጋፍ ሁሉ ተደርጎላቸው በወቅቱ የሚፈልጉትን መሬት ወስደው ግንባታ ጀምረው ያልጨረሱና ከሚገባው በላይ የተጓተቱ እንዲሁም ግንባታ ጨረወሰው ወደ ሥራ ያልገቡና ለረዥ ጊዜ የቆዩ ፕሮጀክቶች አሉ፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ የሌሎች ባለሀብቶችን የማልማት ዕድል ከማጥበቡም ባሻገር በሀገር ደረጃ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት እንቅፋት ነው፡፡ ስለዚህ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው በውላቸው መሠረት ወደሥራ ያልገቡ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወይም ባለሀብቶችን በመለየት አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ መውስድ አስፋላጊ ነው፡፡ ይህንኑ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ይህን ሰነድ ማዘገጀት አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቷል፡፡

ይህ የዳሰሳ ጥናት በስድስት ክክልሎች ላይ የተካሄደ ሲሆን፣ በንዑስ ዘርፉ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው በተለያየ ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች (ባለሀብቶች) ዝርዝር መረጃ አካቶ ይዟል፡፡ በጥቅሉ ሰነዱ እንደ ሀገር ወጥ የሆነ ወሳኔ ለመስጠት፣በቀጣይም ግልፅ፣ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 2. ዓላማ

- የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ወይም ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ያልገቡ የኢንደስትሪ ፕሮጀክቶችን  ለመለየት
- የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶቹን  መሠረታዊ ችግሮችና ምክንያቶች ለማወቅ
- ለወሳኔ የሚረዱ በቂ መረጃ ለማደራጀትና ጉዳዩ ለሚመለከተው የበላይ አካል በማቅረብ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚሉ ናቸው፡፡

## 3. የዳሰሳ ጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ዳሰሳ ጥናት አስፈላጊነት፣በየክልሉ የኢንቨስትመንት መሬት በመውስድ ግንባታ ጀምረው ያቆሙ ወይም ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ያልገቡ የኢንደስትሪ ፕሮጀክቶችን በመለየትና ገላጭ መረጃ የያዘ ሰነድ በማደራጀት፣ተገቢና ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

## 4. የዳሰሳ ጥናቱ ወሰን (Scope)

ይህ ሰነድ በስድስት ክልሎች (ትግራይ፣አማራ፣ኦሮሚያ፣ሶማሊ፣ደቡብና ሐረሪ) እና በአንድ ከተማ መስተዳደር (ድሬዳዋ) ውስጥ የሚገኙ በንኡስ ዘርፉ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ግንባታቸውን ወይም ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ያልገቡ ነባርና አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና ኢንደስትሪዎችን የሚያካትት ነው፡፡

## 5. በንዑስ ዘርፉ የተሰማሩ መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ ኢንደስትሪዎች መረጃ

### 5.1. በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ያልጀመሩ(ማልማት ያልቻሉ) ፕሮጀክቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ዞን | ወረዳ | ከተማ | የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ | የመሬቱ መጠን (ሄ/ር) | የተሰጠበት ና ውል የተፈጸመበ | ያለው ካፒታል | Project status | የስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቡያሲር ቁራ (መሐመድ ሰይድ) የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | እንሰሳት ማደለብና የሥጋ ማቀነባበሪያ | 10 | 08/12/2001 | | ለውሳኔ የቀረበ | |
| 2 | ሜየር አፍሪካ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | 1 | 14/07/03 | | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ | |
| 3 | አብዱልለጢፍ አብዱልሀሚድ የሥጋማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | 1 | 25/07/04 | | ግንባታ እያለ የቆመ | |
| 4 | ጋሚ መሀመድ ሞሀሰን መንሱር የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ምስራቅ ሸዋ | ኡርባ | ወለን ጨቲ | የእንስሳት ማድለብና ሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | 2.00 | | 80000000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ | |
| 5 | መሀመድ አቡዲያቢ ካምፓኒ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የእርባታ እንቁላል ምርትና የዶሮ ማቀነባበሪያ | 50 | 15/7/1996 ና 1/5/2001 | 210,000,000 | ሥራ ጀምሮ ያቆመ | 114401319 |
| 6 | ጀልቀባ አግሮ ኢንዱስትሪ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የዶሮ እርባታና ማቀነባበሪያ | 0.5 | 22/01/02 | | በግንባታ ላይ ያለና ማስጠንቀቂያ | |
| 7 | በድሩ መሀመድ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | አግሮ ፕሮሰሲንግ | 0.25 | 7/11/1999 | | በግንባታ ላይ ያለና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው | |
| 8 | ጌታሁን አላሚር | ምስራቅ ሸዋ | አጄሬ | አዲስ ዓለም | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.493 | 10/6/2001 | 1000000.00 | በግንባታ ላይ ያለ | O9112154 92 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | ያሞስ ቢዚነስ ኃ.የተ የግል ድርጅት | ምዕራብ ሸዋ | ኡርባን | አጄሬ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 1.10 | | 60000000.00 | ሥራ ያልጀመሩ(Pre-implementation) | |
| 10 | ሞጁዱ አህመድ | ደ/ምዕ/ ሸዋ | ኢሉ | ቡቲ ታልጎ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 1.50 | | 30055000.00 | ሥራ ያልጀመሩ(Pre-implementation) | |
| 11 | ጆ አማረ ኃ.የተ. የግል ድርጅት | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ሱ. ሐዋስ | ዲማ ማኞ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.501 | 23/10/00 | 300000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) | 911995241 |
| 12 | ናትናኤል የማና | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ሱሉልታ | አቢቹ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.9876 | 30/03/00 | 9348236.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) | 911601740 |
| 13 | ኒኒ ግዛቸው | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ሱሉልታ | ማሊ ማ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 1.5 | 13/02/05 | 4000000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Constru.) | 911898121 |
| 14 | ሃና አየለ | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ሱሉልታ | ገልዬ ከታ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 2.42 | 28/04/06 | 4000000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ | 913880141 |
| 15 | ትግስት አለሙ | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ሱሉልታ | ሱሉ ልታ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 1.5 | 7/9/2004 | 30220000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) | 911200730 |
| 16 | ጀማል ኢብራሂም | ምስ.ሸዋ | ቢሾፍቱ | ቢሾፍ ቱ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 1.000 | 12/11/1999 | 1304000.00 | ምንም ያልጀመረ | |
| 17 | ወየራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ.የተ. የግል ድርጅት | ምስ.ሸዋ | ቢሾፍቱ | ቢሾፍ ቱ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.53 | 27/6/99 | 5400000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under | |
| 18 | ቡዛየሁ ይርጋ | ምስ.ሸዋ | ሞጆ | ሎሜ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.7 | 28/01/97 | 4000000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under | 0911514576 |
| 19 | አረጋሽ ንጋቱ | ምስ.ሸዋ | ሞጆ | ሎሜ | ወተት ማቀነባበሪያ | 0.5 | 28/04/02 | | ግንባታ ላይ እያለ የቆመና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው | |

## 5.2 ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የባለሀብት ስም | የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ | ያስመዘገበው ካፒታል | የተሰጠበት ቀን(ዓ.ም) | የሚፈጥረው የስራ ዕድል | | | ስልክ ቁጥር | የዕድሳት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ቋሚ | ጊዜዊ | ድምር | | |
| 1 | አቶ ጀማል ሙሳ አብዱላሂ | የከብት እርባታና የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ | 1,374,674 | | 13 | 5 | 18 | 911032712 | |
| 2 | አይናለም ካሳዬ | የከብት እርባታና የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበሪያ | 6,518,013 | | 10 | 16 | 26 | 915992586 | |
| 3 | ይርጋለም አበበ | የወተት ከብት እርባታና የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ | 1,500,000 | | 37 | 20 | 57 | 911498692 | |
| 4 | ዳዊአብ የወተት ውጤቶች ማቀነባበርያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ | 6,900,000 | | 30 | 10 | 40 | 911652456 | |
| 5 | ቴዎድሮስ አምዴ | ወተትና የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ | 1,707,310 | | 36 | | 36 | 915730107 | |
| 6 | አበራ ሂርዳሳ | የወተት ከብት እርባታና የወተት ዉጤቶችማቀነባበሪያ | 1,638,506 | | 21 | 15 | 36 | 939890191 | |
| 7 | አሚር ሙክታር | ወተት ማቀነባበርያ | 15,000,000 | | 55 | | 55 | 920824377 | |
| 8 | አንዋር ሀሰን | የወተት ተዋፅዎ ማምረቻ | 10,000,000 | | 41 | - | 41 | 929479944 | 22/10/2009 |
| 9 | አብዱረህማን ጠሀ | የወተት ተዋፅኦ | 10,000,000 | | 41 | - | 41 | | |
| 10 | ሼክ ሀቢብ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ወተትና የወተት ተዋፅዎ ማቀነባበርያ | 60,000,000 | | 84 | 42 | 126 | 911211726 | |

## 5.3. በትግራይ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የባለቤቱ ሥም | የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ | የተሰጠበት ቀን | የሚገኝገኝበት ወረዳ | ወደ ሥራ የገባበት ጊዜ | የመሬት መጠን(ሄ/ር) | ያለው ካፒታል | ሊቀጥር ያሰበው ሠራተኛ ብዛት | | | አሁን ያለበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ቋሚ | ጊዜያዊ | ድምር | |
| 1 | ዠፋን ካህሳይ ገ/መድኅን | የወተት ማቀነባበሪያ | 22/11/07 | ሰቲት ሁመራ | 2010 | 0.2 | 2,010,000 | 9 | 20 | 29 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 2 | ትግራይ ጄኔራል የንግድ ፌዴሬሽን | የሰሊጥና ማር ማቀነባበሪያ | 12/8/2003 | ሰቲት ሁመራ | 2004 | 1 | 31,152,500 | 14 | 50 | 64 | ምንም እንቅ.የሌለው |
| 3 | ቦክራ ዩንዬንን | የወተት ማቀነባበሪያ | 23/5/2008 | ማጨው | | 0.3 | 8,480,000 | 36 | 13 | 49 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 4 | አብርሃም ገ/ኢግዚአብሔር | የእንሰሳት እርባታና የወተት ማቀነባበሪያ | 28/8/2008 | ሺራሮ | 2009 | 25 | 5,000,000 | 15 | 30 | 45 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 5 | አራዶም ቢዚነስ ጠቅላላ ንግድ ድርጅት | የማር ምርት ማቀነባበሪያ | 22/4/07 | ሺሬእንደ ስላሴ | 2012 | 0.06 | 5,000,000 | 29 | 4 | 33 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 6 | መገች ጠቅላላ የንግድ ድርጅት | የወተት ማቀነባበሪያ | 7/1/2007 | ሺሬ እንደ ስላሴ | 2012 | 0.5 | 14,456,145 | 54 | 15 | 69 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 7 | አራያ በላይ ገዛኸኝ | አግሮ ፕሮሰሲንግ | 15/09/97 | ሺሬ እንደ ስላሴ | 2001 | 0.506 | 3,830,000 | 3 | 12 | 15 | ምንም እንቅ.የሌለው |
| 8 | መሃሪ አብርሃ | የማር ምርት ማቀነባበሪያ | 7/11/2006 | ውቅሮ | 2009 | | 6,500,000 | 20 | 15 | 35 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 9 | ጌታቸው አርአያ ደስታ | የማር ምርት ማቀነባበሪያ | 6/12/2006 | አጽቢ | 2009 | | 20,932,500 | 29 | 0 | 29 | ቅድመ ትግበራ ላይ |
| 10 | ፀሐይ ታደሰ ገ/መድኅን | የወተት ማቀነባበሪያ | 29/06/02 | ውቅሮ | 2003 | 1 | 1,500,000 | 4 | 3 | 7 | ምንም እንቅ.የሌለው |

## 5.4. በአማራ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ

### በክልሉ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ወስደው ቦታ የተሰጠቸው እና ቅድመ ግንባታ ላይ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ /የባለቤቱ ስም | የተሰማራበት የሥራ/የምርት ዓይነት | የፕሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ(ከተማ) | የተረከበው የመሬት መጠን(በካሬሜ | የተቋቋመ በት ዓ.ም | የተቋቋመበት ካፒታል/000/ | አሁን ያለበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አንዱ አለም ሃይሌ | የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 20 00 | 2006 | - | የኢንቨስትመንት ፍቃድና መሬት ወስደው በተለያየ ምክንያት ምንም ሥራ ያልጀመሩና ጀምረውም ያቆ ናቸው:: |
| 2 | የሱፍ አበራ | የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 10000 | 2007 | 5831536 | |
| 3 | ፌብስሙ አግሮ ኢንዱስትሪ | ሥጋ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 5000 | 2008 | 38240790 | |
| 4 | አንደሙብ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | የዶሮ ሥጋ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 10000 | 2007 | 6317100 | |
| 5 | ደጅኻማች የሱፍ መታሰቢያ | የዶሮ ሥጋ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 15000 | 2007 | 30000000 | |
| 6 | የሱፍ አዱኛ ካሣየ | የዶሮ ስጋ እና የግብርና ውጤቶች | ኮምቦልቻ | 10000 | 2007 | 38700000 | |
| 7 | ከድፋር ኃ/የተ/የግል ማህበር | አሣ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 5000 | 2007 | 42000000 | |
| 8 | ኮምቦልቻ ዶሮ ሃብት ልማት ኢንተርፕሪዝ | የዶሮ ሥጋ ማቀነባበሪያ | ኮምቦልቻ | 20000 | 2007 | 19052232 | |
| 9 | ኢስት ዌስት | የተቀነባበረ ስጋ | ኮምቦልቻ | 15000 | 2008 | 52000000 | |
| 10 | መሰረት መላኩ ደሳለኝ | የተቀነባበረ ሥጋ | ኮምቦልቻ | 10000 | 2007 | 19615770 | |
| 11 | ዳኛው ያውቃል | ሥጋ ማቀነባበር | ሀ/ማሪያም ከሰም | 1ሄ/ር | 27/01/2008 | 47173350 | |
| 12 | እሸቱ በለጠ | ሥጋ ማቀነባበር | ሀ/ማሪያም ከሰም | 5ሄ/ር | 12/10/206 | 5000000 | |
| 13 | ቡሬ የእንስሳት ማቀነባበሪያ ሀ/የተ/የግ/ማ | መኖ ማቀነባበሪያ | አንጎለላ ጠራ | 5ሄ/ር | 8/2/2008 | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ስደት ይብቃ | መኖ እና ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ | አንጎለላ ጠራ | 3ሄ/ር | | | የኢንቨስትመንት ፍቃድና መሬት ወስደው በተለያየ ምክንያት ምንም ሥራ ያልጀመሩና ጀምረውም ያቆ ናቸው። |
| 15 | ዩሀንስ አስጨናቂ | ሥጋ ማቀነባበሪያ | ደ/ብርሀን | 1ሄ/ር | | 7.959.000.00 | |
| 16 | አሚናት ሀሚድ አሊ | የዶሮ ሥጋ ማቀነባበሪያ | ደ/ብርሀን | 0.5 | | 23.000.000.00 | |
| 17 | ቢጃይ ናይከር | የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ | ደ/ብርሀን | 0.5 | | 10.000.000.00 | |
| 18 | ማይኔክስ/ ሞርኒግ ስታር/ | የሥጋ ማቀነባበሪያ | ደ/ብርሀን | 0.5 | | 7.900.000.00 | |
| 19 | ማራአለም ጎንደር ንግ/ሥ/አ/የተ/የግ/ማ | የሥጋና ወተት ውጤቶች ማምረቻ | ጎንደር | 0.15 | 2006 | 5,648,000 | |
| 20 | ደማስ አግሮ ኢንዱስትሪ ፒኤል | የማር ውጤቶች | ጎንደር | 1.5 | 2006 | | |
| 21 | ዘነብወርቅ መንግስቱ | የአሳ ማቀነባበሪያ | ጎንደር | | 2002 | 1,450,000 | |
| 22 | NTT Agricvlture &Trady PLC | የስጋ ማቀነባበሪያ | ጎንደር | 0.3 | 2007 | | |
| 23 | ፒጋሲ የማር ማቀነባበሪ | የማር ማቀነባበሪያ | ጎንደር | 0.2 | 2007 | | |
| 24 | ጉሹ ፀጋው | የመኖ ማቀነባበሪያ | ጎንደር | 0.29 | 2007 | | |
| 25 | ሀብቴ አበራ ግዳይ | የዶሮ ውጤቶች ማቀነባበሪያ | ጎንደር | 0.35 | 2007 | | |
| 26 | ዱከም | ሥጋና የስጋ ውጤቶች | ደ/ማ | 100 | 2007 | 1700000 | |
| 27 | ህብር የእንሰሳት ተዋፅኦ ማቀነባበሪያ | የእንስሳት ተዋፅኦዎች | ደ/ማ | - | 2008 | 16717000 | |
| 28 | እንዳልካቸው አልማው | ማርና የማር ውጤቶች | ደ/ማ | 250 | 2008 | 21882271 | |
| 29 | ሀይማኖት እርቁ | ማርና የማር ወጤቶች ማቀነባበሪያ | ደ/ታቦር | | | | |
| 30 | አለልታሰብ መክብብ | የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ | ደ/ታቦር | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 31 | ኤልያስ አወል | የስጋዉጤቶችማቀነባበርያ ፋብርካ | ባቲ ከተማ | 2000ካ/ሜ | 2008ዓ.ም | 12ሚ | የኢንቨስትመንት ፍቃድና መሬት ወስደው በተለያየ ምክንያት ምንም ሥራ ያልጀመሩና ጀምረውም ያቆ ናቸው። |
| 32 | አድማስ ዩኒዮን | የእንስሳት መኖ | እንጅባራ | 20000 | 2007 | 20510000 | |
| 33 | መልካሙ ምኒችል | የእንስሳት መኖ ማቀናበር | አዴት | 10000 | 2008 | | |
| 34 | ጃቢ ጥምር አግሮ ፕሮሰሲንግ | ሥጋና የስጋ ውጤቶች | | 100000 | | | |
| 35 | አሚኑት ሃሚድ | የደሮ ሥጋ ማቀነባበር | ›› | 3000 | 2007 | | |
| 36 | ታረቀኝ አለሙ ሃሰን | አሳ ማቀነባበር | ›› | 3000 | 2007 | | |
| 37 | መስፍን መንግስቱ | ወተት፣አሳ፣ሥጋ ማቀነባበር | በ/ዳር | 5000 | 2008 | | |
| 38 | ፉአድ ሰይድ | የዶሮ ሥጋ ማቀነባበር | ደሴ | | 2008 | 1,850,000 | |
| 39 | ዳንኤል አወቀ አለማየሁ | የደሮስጋ ማቀነባበር | ደሴ | | 2006 | 6,000,000 | |
| 40 | ኢብራሂም አደም | የደሮስጋ ማቀነባበር | ደሴ | | 2008 | 2,000,000 | |
| 41 | ቴኮብ ትሬድንግ | ሥጋ ማቀነባበሪያ | ራያ 3/25/2004ቆቦ | | 2008 | 300 | |
| 42 | አሸራፍ ኢንዱስትሪያል ግሩፕ የግል ካምፓኒ | የሥጋ፣የዓሣ እርባታና ማቀነባበርያ | ባህዳር | 12951000.00 | 2004 | | |

## 5.5. በሀረሪ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የባለሀብቱ ስም | የተሰማራበት የሥራ/የምርት ዓይነት | ካፒታል | የምስክር ወረቀት ያገኘበት ቀን | አሁን ያለበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወንድሙ ፈይሳ | የወተት ውጤቶች ማቀነባበር | 397,107 | 2/10/1989 | የኢንቨ. ፍቃድና መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ እንዱስትሪዎች |
| 2 | አዜብ ይደሩ ተገኝ | የወተትና የወተት ምርቶች ማቀነባበሪያ | 320,000 | 18/12/2002 | |
| 3 | ዘካሪያ ኢብራሂም | የወተትና ዶሮ እርባታና ማቀነባበሪያ | 5,241,990 | 21/13/2002 | |
| 4 | ቱርጫን ኦርጋኒክ የሥጋ ማቀነባበሪያ ኃ.የተ.ካምፓኒ | የእንስሳት እርባታ፣ማወፈርና ሥጋ ማቀነባበሪያ | 181,000,000.00 | 3/5/2004 | |
| 5 | ኢንጂነር ሱልጣን አደም | አግሮ የንግድና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ | 767,239 | 2/11/2005 | |

# 5.6. በደቡብ ክልል የሚገኙ የኢንቨስትመንት መሬት ወስዶ ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የባለ ሀብቱ ስም | የተሰማራበት የሥራ/የምርት ዓይነት | የሚገኝበት ቦታ | | የተሰጠው መሬት መጠን | መሬቱ የተሰጠበት ቀን | ያለው ካፒታል | የሠራተኛ | | አሁን ያለበት ሁኔታ | የስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዞን | ወረዳ | | | | የታሰበ | አሁን ያለው | | |
| 1 | እመቤት ዋዳ | የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ | ወላይታ | ሶዶ ዙሪያ | | 10/24/2002 | 4,905,492.00 | 24 | | የለቀቀ | |
| 2 | ግዛቸው መኮንን | የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ | ሲዳማ | አላታ ወንደ | 2 | 3/17/2000 | 1,228,767.00 | 67 | | ቅድመ ትግበራ | 465513368 |
| 3 | አሽራፍ ግብርና ኃ.የተ. ካምፓኒ | የእንሳሳት እርባታ ፣ማድለብና የሥጋ ማቀነባበሪያ | | | | 10/29/2009 | 36,000,000.00 | 200 | | የለቀቀ | 910318180 |
| 4 | ሙላት ታዬ አንጋሳ | እንሳሳት ማድለብና ወተት | ሲዳማ | ዳራ | | 1/15/2006 | 10,690,000.00 | 63 | 0 | የተመዘገበ | |
| 5 | ዘለቀ ዓለማየሁ | ወተት ማቀነባበሪያ | ወላይታ | ሶዶ | | 8/18/2003 | 1,000,000.00 | 17 | 0 | የለቀቀ | 911744078 |
| 6 | ዋይድ ላንድ ኢንቨ.ኢትጵያ ኃ.የጠ.ካምፓኒ | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያ | ጋሞ ጎፋ | አርባምንጭ | | 12/3/1991 | 12,569,730.40 | 83 | | ሥራ ላይ የሌለ | 911831175 |
| 7 | ታሪግ አህመድ መሀመድ | የዓሣና ድንች ማቀነባበሪያ | | | | 7/31/2008 | 1,413,500.00 | 41 | 0 | የለቀቀ | |
| 8 | ቦኖሻ የዓሣ እርባታና የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያና የተቀናጀ ግብርና | ሀዲያ | ሻሺጎ | 50 | 9/13/2002 | 878,590.00 | 72 | 0 | በግማሽ ሥራ ላይ ያለ | 911930022 |
| 9 | ፎኒያ የዓሣ ና ሥጋ ማቀነባበሪያ | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያ | | | | 7/7/2009 | 13,245,000.00 | 70 | | የለቀቀ | |
| 10 | የሺሃረግ ሶሎሜ ምትኩ | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያ | | | | 1/3/2010 | 20,000,000.00 | 130 | | የለቀቀ | 911208581 |
| 11 | ቶማስ አንተኒ ራይደር | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያ | | | | 4/19/2005 | 3,700,000.00 | | | ቅድመ ትግበራ | 911655958 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ካሊድ ሞሂልዲን ባክሂት ፋድላላ | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያ | | | | 8/13/2005 | 3,000,000.00 | | | የተመዘገበ | |
| 13 | አል ዘሃራኒ ሳላህ ጂም | የዓሣ ምርት ማቀነባበሪያ | | | | 6/21/2007 | 1,000,000.00 | 25 | | የለቀቀ/የተወ | |
| 14 | ማጊድ ኢብራሂም ኢድሪስ | የዓሣ እርባታና ማቀነባበሪያ (ለኤክስፖርት) | | | | 4/11/2007 | 2,000,000.00 | 45 | | የለቀቀ/የተወ | 912093255 |
| 15 | ዱራሜ የወተትና ወተት ተዋጽኦ ምርት ማቀነባባሪያ ኃ.የተ የግል ካምፓኒ | የወተትና ወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ | ኬቲ | ዱራሜ | | 12/15/2006 | 25,000,000.00 | 243 | 0 | የተመዘገበ | 911902253 |
| 16 | መሀመድ አወል አብዲቁ | የወተት ማቀነባበሪያ | አሳባ | አሳባ | 0.028 | 1/24/1999 | 820,000.00 | 44 | | ቅድመ ትግበራ ላይ | 911534610 |
| 17 | ዝናሽ ዳንኤል | የወተት ማቀነባበሪያ | ወላይታ | ሶዶ ዙሪያ | | 1/30/2007 | 2,500,000.00 | 23 | 0 | የለቀቀ/የተወ | 461104774 |
| 18 | ደረጀ ታምሬ | የወተት ማቀነባበሪያ | ጉራጌ | መስቃን | | 4/3/2000 | 1,367,000.00 | 60 | 12 | የለቀቀ/የተወ | 916733490 |
| 19 | ኤየለ ተዘራ | ዘመናዊ የሥጋ ማቀነባበሪያ | ጋሞ ጎፋ | አርባ ምንጭ ዙሪያ | | 1/8/1999 | 5,000,000.00 | 41 | | የለቀቀ/የተወ | 112766271 |
| 20 | ጆይ ሪቨር የሥጋ ምርት ኃ.የተ.የግል ካምፓኒ | የዶሮና እንሳሳት እርባታና ማድለብ እና ሥጋ ማቀነባበሪያ | | | | | 1,680,000.00 | | 0 | የለቀቀ/የተወ | 463312836 |

## 6. በ2009 ዓ.ም ሁለተኛ ግማሽ ዓመት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት እርምጃ ለመውሰድ የተለዩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች

በዚህ በጀት ዓመት ቀደም ሲል የኢቨስትመንት መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ እንዱስትሪዎች ላይ እርምጃ ለውስድ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡ ይህንንኑ ዕቅድ ለመተግበር በቀጣይ ግማሽ ዓመት በዳሳሳ ጥናቱ ከተለዩት ውስጥ ቀጥሎ ያሉት ስምንት ኢንዱስትሪዎች ላይ ትኩረት ተሠጥቶ ይሠራል፡፡ ሥራውን በአጭር ጊዜ ለመፈጸም ይቻል ዘንድ ለጊዜው ከቅርበት መጀመሩ አስፈላጊ በመሆኑ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን የሚገኙት ብቻ ተለይተዋል፡፡

<u>በዚህ በጀት ዓመት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት እርምጃ ለመውሰድ የተለዩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች መግለጫ ሰንጠረዥ</u>

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ዞን | ወረዳ | ከተማ | የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ | የመሬቱ መጠን | መሬቱ ተሰጠበትና ውል | ያለው ካፒታል | Project status | የስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሜየር አፍሪካ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | 1 | 14/07/03 | | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ | |
| 2 | አብዱልለጢፍ አብዱልሀሚድ የሥጋማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | 1 | 25/07/04 | | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ | |
| 3 | ጀልቀባ አግሮ ኢንዱስትሪ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | የዶሮ እርባታና ማቀነባበሪ | 0.5 | 22/01/02 | | በግንባታ ላይ ያለና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው | |
| 4 | በድሩ መሀመድ | ምስራቅ ሸዋ | ሎሜ | ሞጆ | አግሮ ፕሮሰሲንግ | 0.25 | 7/11/1999 | | በግንባታ ላይ ያለና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው | |
| 5 | ጀ አማረ ኃ.የተ. የግል ድርጅት | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ሱ. ሐዋስ | ዲማ ማኛ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.501 | 23/10/00 | 300000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) | 911995241 |
| 6 | ወየራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ.የተ. የግል ድርጅት | ምስ.ሸዋ | ቢሾ ፍቱ | ቢሾፍቱ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.53 | 27/6/99 | 5400000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) | |
| 7 | ቡዛየሁ ይርጋ | ምስ.ሸዋ | ሞጆ | ሎሜ | የወተት ከብት እርባታና ወተት ማቀነባበሪያ | 0.7 | 28/01/97 | 4000000.00 | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) | 0911514576 |
| 8 | አረጋሽ ንጋቱ | ምስ.ሸዋ | ሞጆ | ሎሜ | ወተት ማቀነባበሪያ | 0.5 | 28/04/02 | | ግንባታ ላይ እያለ የቆመ (Under Construction) ማስጠንቀቂያ የተሰጠው | |

## 7. የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ባልጀመሩ በፕሮጀክቶቹ ባለቤቶች የሚነሱ ዋና ዋና ምክንያቶች/ችግሮች

የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው የግንባታ ሥራ ያልጀመሩ ወይም ግንባታ ጀምረው ያቆሙ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ባለቤቶች የግንባታ ሥራቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ ለምን እንዳልገቡ ሲጠየቁ የሚያቀርቡት ምክንያቶች አጥጋቢ አይደሉም፡፡ በአብዛኛው እንደምን ብለው መሬቱን በእጃቸው ካስገቡና ትንንሽ ግንባታ ከጀመሩ በኋላ ሲፈለጉም በአካባቢው አይገኙም፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ግንባታም ካጠናቀቁ በኋላ ግልጽና አጥጋቢ ባልሆኑ ምክንያቶች ዛሬ ነገ በማለት እያንተቱ ይገኛሉ፡፡

ያም ሆነ ይህ እነዚህ ባለሀብቶች በአብዛኛው የሚያቀርቡት ምክንያቶች ውስጥ ከዚህ በታች የተገለጹትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህም፡-

1. የማስፋፊያ መሬት አቅርቦት ጥያቄ በወቅቱ መልስ አላማግኘትና ሃሳብን ለመቀየር ሲባል የማመንታት ሁኔታ መኖሩ
2. በራሳቸው ያላቸው የፋይናንስ አቅም ውስንነትና ከባንክም የጠየቁት ብድር በወቅቱ አለመለቀቅ፣
3. በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል አለማግኘትና ሲገኝም በብዛት ስለሚቆራረጥ ለወደፊት ቀጣይ ሥራ እምነትና ድፍረት የማጣት
4. በቂ የውሃ መስመር ያለመዘርጋት ለሥራ ችግር መሆኑ
5. በጥቅሉ ሲታይ ላሉብን ችግሮች ለሚለከታቸው ለተለያዩ የየክልሉ አካላት ስናመለክት ለረጅም ግዜ ምላሽ አናገኝም የሚሉ ኛቸው፡፡

## 8. በየክልሉ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ባልጀመሩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት በሚደረግ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የፍትሄ እርምጃዎች

### 8.1. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

በየክልሉ ለመገንዘብ እንደተቻለው የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ባልጀመሩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት የሚደረገው ክትትል አናሳ ነው ማለት ይቻላል፡፡ መሬት ሰጥቶ ከማየት በስተቀር ይሄ ነው የሚባል ተከታታይነት ያለው ክትትልና

ድጋፍ ተደርጓል ለማት አያስደፍርም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በግልጽ ዘርዝሮ ለማስቀመጥ አልተቻልም፡፡ ይሁንና ባለሀብቱ መሬት ከወሰደ በኂላ እያደር ፍላጎቱ እየቀነሰ መምጣቱና አሳማኝ ያልሆኑ ምክንየቶችን መደርደር በዋናነት ሊጠቀስ የሚችል ችግር መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 8.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ከላይ እንደተገለጸው በክልሉ ተከታታይነትና ወጥ የሆነ ክትትል ባለመደረጉ በኢነቨስትመንት ሕጉ በሚያዘው መሠረት ጊዜውን ጠብቆ የተወሰደ ተጨባጭ እርምጃ በአብዛኛው ማየት አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ ክልሎች ባለሀብቱን ጠርቶ የማሳወቅ፣የማጀመሪያ ማስጠንቀቂያ የመስጠትና አንዳንዶቹን ለኢንቨስትመንት ቦርድ ኮሚቴ ውሳኔ የማቅረብ እርምጃ ወስደዋል፡፡ ከየክልሎቹ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች መረዳት እንደተቻለው ወደፊት መረጃዎች በትክክል ተጣርተው ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በኢንቨስትመንት ሕጉ መሠረት እንደ አስፈላጊው እርምጃ እንደሚወስድና መሬቱ ለሌላ አልሚ ባለሀብት ተላልፎ ለሰጥ እንዲሚችል አመላክተዋል፡፡

## 9. ማጠቃለያና አስተያየት

የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መንግስት ባወጣው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረት በንዑስ ዘርፉ ለተሳማሩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እያደረገ ይገኛል፡፡ በተለይም የውጭ ምንዛሪን ለማሳደግ ለኤክስፖርት ድርጅቶች እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በአገር ውስጥ ምርት መተካትና በውጭ ምንዛሪ የሚገዙትን ማስቀረት (Import substitution) ላይ የተሰማሩ ኢንዱሰትሪዎችን ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡ በሌላ በኩል የንዑስ ዘርፉን የኢንዱስትሪ ልማት የበለጠ ለማስፋፋት አዳዲስ ኢንቨስትንትመንቶችን የመሳብ፣የመደገፍና ሥራ ውስጥ የማስገባት ሥራ ሲያከናውን በአንጻሩ የኢንቨስትመንት መሬት ወስድው ወደ ሥራ ያልገቡትን በመከታተልና በማጣራት አስፈላጊው ግርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

ስለዚህ በንኡስ ዘርፉ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ወደ ግንባታ ሥራ ያልገቡ ወይም ግንባታ ጨርሰው ሥራ ያልጀመሩ ባለሀብቶች የዳሳሳ ጥናት በማድረግ ለመለየት ጥረት

ተድርጓል። የዳሰሳ ጥናቱ በስድስት ክልሎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር የተደረገ ሲሆን የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል በንኡስ ዘርፉ በፕሮሰሲንግ ለመስማራት መሬት ወስዶ ወደ ስራ ያልገባ አንድም የኢንዱስትሪ  ፕሮጀክት እንደሌለ ታውቀዋል። በዚህ የዳሰሳ ጥናት ከተገኙ ጥቅል መረጃዎች በንኡስ ዘርፉ ለመሰማራት በየክልሉ የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ሥራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች እንዲሁም ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ሳይገቡ ለረጅም ጊዚያት የቆዩ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ፕሮጀክቶች ተካተዋል።

በአጠቃላይ ይህ ሰነድ ከሞላ ጎደል በተጠኑት ክልሎች ያለውን መረጃ አካቶ የያዘ በመሆኑ ለታሰበው ሥራ ያለው ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ስለዚህ በቀጣይ በየደረጃው ለሚወስዱ እርምጃዎች እንደመነሻ ሊጠቅም ይችላል። የዚህ ዓይነት ትክክለኛ መረጃ የንዑስ ዘርፉን ኢንቨስትመንት ማስፋፋትና ለማቀላጠፍ ብሎም ጤናማና ውጤታማ ፕሮጀክቶችን ለማበረታታት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ወደፊት በየጊዜው የሚሻሻል ይሆናል።


ለኢንቨስትመንት የተወሰደ መሬት፣ታጥሮ  ወይም ግንባታው ተጀምሮ ሙሉ ለሙሉ ሳይጠናቀቅ የቆመ ብዙ አለ ። በተለይ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ከዱ.ዘ /ሞጆ አካባቢ ይበዛል።ቢታኝ!